# ቴዎድሮስና ፈተናው

ሥነጽሁፋዊ ሂስ

የዚህን ሥነፅሁፋዊ ሂስ ርዕስ ለተመለከተ ተደራሲ ቴዎድሮስ ደግሞ ምን ፈተና አለበት? የኢትዮጵያን አንድነት ጥያቄ ሕይወትን በሚያህል ክቡር መስዋዕትነት መልሶ የራስንም የሃገርንም ወቅታዊ ፈተና በብቃት የማለፍን አርአያነት በገፀ - በረከትነት ለትውልድ ያበረከተ ድንቅ ጀግና...ደግሞ ለቴዎድሮስ የምን ፈተና...ፈተናስ የዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ ፈተና...ሳያሰኝ አይቀርም። አዎን ሃዲስ ዓለማየሁ ( ገጽ 24 ) እና ብዙዎች እኩዮቻቸውን...

...ልጆች ሁሉ ወላጆች እንዳሏቸው ግልፅ ነው። ነገር ግን የስጋ መወለድ
ብቻ ልጆችን ሙሉ በሙሉ የወላጆቻቸው ልጆች አያደርጋቸውም። ...

ያሰኘ - የወላፈንዲ ስልቻ ዘመን። የወላፈንዲ ስልቻ ጤፍ ይይዛል ስንዴ አይዝም አሉ - የቸገረ ነገር ።

ውድ ተደራስያን÷

ነገርን ነገር ያመጣዋል ሆኖ እንጂ የዚህ ሥነፅሁፋዊ ሂስ ዓላማ በኢትዮጵያ አንድነት አባት በአፄ ቴዎድሮስ የሕይወት ዘመን ፈተና ላይ ያተኮረ አይደለም። ይልቁንም ደራሲ ቴዎድሮስ አበበ በቅርቡ ባበረከተልንና " ፈተና " ሲል በሰየመው የግጥም መድበል ላይ ነው - ያነጣጠረው።

እናት ሃገርን ያህል - ያውም ውዷቱን ኢትዮጵያ - ሳታስቀይመኝ አስቀይሜ ትቻት በወጣሁ በአስራ አምስተኛው ዓመት - ትዝ ይለኛል - በፈረንጆቹ ሁለት ሺህ ሰድስት በጋ ወራት ላይ - ገፍቼው የመጣሁትን እንጀራ ፍለጋ ወደ ፈረንጆቹ ሃገር የኢትዮጵያ መደብር ገብቼ ሳማትር ነው " ፈተና" ን ከእንጀራ ጋር እኩል ተደርድሮ ያገኘሁት። እንጀራና ሥነፅሁፍ ለሽያጭ ተደርድረው መመልከቴ ቢገርመኝም እስካሁን ያልተዋጡልኝን ሁለቱን ፍላጎቶቼን ባንድ ላይ ስላገኘኋቸው ተደስቼ ብድግ ብድግ አደረግኋቸው - በፍጥነት። ታድያ የእንጀራው ዋጋ በግልጥ የእንጀራን ቅርፅ በያዘ ክብ ወረቀት ላይ የተሰራበት ጥሬ ነገር ሳይቀር በዝርዝር ተፅፎ በማየቴ " እንጀራ ያለሃገሩ ተከበረሳ? " ስል ጠየቅሁት - ራሴን። የግጥም መድበሉን የ " ፈተና "ን ዋጋ ለማወቅ ሳገላብጥ ብውል ግን ፍፁም አልሳካልኝ አለ። ድሮስ ቢሆን ፈተና የሚያስከፍለው ዋጋ አስቀድሞ ቢታወቅ ማን ወደ ፈተና ይገባ ነበር?

በነገራችን ላይ ዘመን እንደዛሬው ጠየም ሳይል ( ዘመን ጠቆረ ማለትን ፈራሁ - ዘመነኞች እንዳይቀየሙኝ ) ጥንት ባገራችን እንጀራ መሸጥ ነውር ነበር ይባላል። የዛሬን እንጃ።

ወደ ጉዳዬ ልመለስ÷

" ፈተና " የተሰኘውን የግጥም መድበል ከመደብሩ መደርደሪያ ላይ እንዳነሳሁት ከመቅጽበት ቀልቤን ወደሳበው የመድበሉ ሽፋን ነው አትኩሬ የተመለከትሁት። የፌተናን የፊትና የጀርባ ሽፋኖች ባንድ ላይ ዘርግቼ ለጥቂት ሰከንዶች ሳስተውል ሳላውቀው በምናብ ወደኢትዮጵያዊው ባለሃገር መንደር ጭልጥ ብዬ ተጓዝሁ። ዘመም ያለችው የብዙኃኑ ባለሃገር መኖሪያ ጎጆ ከደጃፏ የቆመው ጥቁር በግና ፈንጠር ብሎ ተዝናንቶ የቆመው ባለብዙ ቅርንጫፍ ዋርካ በተደራሲ አዕምሮ የሚያጭሩት አንዳች ምትሃት አላቸው። በተለይ ከዋርካው ስራ ስሮች ጋር ተጋምደው የተቀመጡት÷

ማንነቴ እንዳይፋቅ
እንዳልረሳ ማንነቷን
ዜግነቴ እንዳይቆሽሽ
እንዳያረክስ መሰረቷን
እኔነቴን እንዳላጣ
ክሕደት ከእርሷ እንዳይነጥቀኝ
የኢትዮጵያ አምላክ ተለመነኝ
ብርቃትም እሷ አትራቀኝ
የኢትዮጵያ አምላክ ፅናት ስጠኝ
ብርቃትም እሷ አትራቀኝ።...

የሚሉት ስንኞች ባዕድ ሃገር ለማረከው ሁሉ ቃለ ምሕላ ሊሆኑ የሚበቁ ናቸው። ስንኞቹ በተለይ ከዋርካው ስረ መሰረት ግርጌ መሰደራቸው ደግሞ ለተደራሲ ያቀረቡትን ሰምና ወርቅ ቅኔ ፍቺ ጥልቀት ሲያመላክቱ ለባለሙያው ምንያህልነት በቂ ምስክሮችም ናቸው።

ከላይ የተደረደሩት ስንኞች ጥልቅ መልዕክት ታድያ ይበልጡን የመድበሉን ገፆች ለማንበብ ጉጉት አሳደረብኝና ማስታወሻን፥ ማውጫን፥ ቀዳሚ ቃልን፣ ምስጋናንና መግቢያን ትቼ እንደደራሲው ሁሉ ... " አቤቱ ረድኤቴ፣ የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን። " ብዬ በመዝሙረ ዳዊት ቅዱስ ቃል በቀጥታ ወደግጥሞቹ የመጀመሪያ ገፅ ተንደረደርሁ።

ደራሲ ቴዎድሮስ አበበ በግጥም መድበሉ ጊዜ ሳያባክን የሚኖርበትን ዘመን ትውልድ በ"ጥያቄ " ሲያጣድፈው ነው የምናገኝ - በድርሰቱ መጀመሪያ።

ለምን ይሆን ይሄ ትውልድ በግፍ ዕንባ መነከሩ?
ህልውናው መሰረቱ በፈተና መታጠሩ
ለምን ይሆን የሀገሬስ አንድነቷ መፋለሱ?
ዳር ድንበሯ መደፈሩ ኬላው በሯ መገርሰሱ
ለምን ይሆን በኔው ዘመን ባንዲራዬ መቀደዱ
ታሪክ ቅርሴ መመዝበሩ ዜግነቴ መዋረዱ
ለምን?
ለምን? ( ገጽ 27 )

እያለ እየተንገፈገፈ የዘመኑን እምብርት ጥያቄ ሲጠይቅና በዘመኑም በራሱም ላይ ምሬቱን በማስተጋባት ነው የሚጀምር - በግጥም መድበሉ።

" በምሬት ጀምሮ በምሬት ይለየን ይሆን? " የሚል ጥርጣሬ አደረብኝና በቀጥታ ወደ መጨረሻው የግጥሙ ርዕስ ተጓዝሁ። ላይ ላዩን በግልቡ የሚባለው የችኩሉ ዘመን አባል ነኝና ከመቅጽበት ከመጀመሪያው ወደመጨረሻው ገፅ በማምራቴ እንደማትቀየሙ ተስፋ አለኝ- ክፉ ልማድ በእንዶድም አይለቅ ይባል የለ በሃገራችን።

ይሁንና የቴዎድሮስ አበበ የመጨረሻው ግጥሙ " ህልም " ህልሜ ሆኖ ከደራሲው ጋር በፈተናም በህልምም የተገናኘንበትን ስንኞች ደጋግሜ አነበብኳቸው። " ሕልም " ነው - የመጨረሻው ግጥሙ ርዕስ። በቁም ሕልሙ...

ምን ትመኛለህ ብትሉኝ
መመኘቴ ካልከፋ
አገር - በቀል ሥርዓት
በኢትዮጵያ ልክ የተሰፋ
ለባህሏ የሚስማማ

የብስ ውሐዋን የሚያለማ
እምነቷን የሚያጸብር
ታሪክ ቅርሷን የሚያከብር
ማኅበራዊ ትስስሯን
የፈሪሀ እግዚአብሔር ውርሷን
የሚያጸና ...
ኢትዮጵያዊ ፍልስፍና
ነው ለማየት የምመኘው
የማልመው:: ...... ( ገጽ 141 )

እያለ ባብዛኛው በባዕድ የሚተማመነውን የራሱን ትውልድ ሸንቆጥ እያደረገ ምክሩን በምኞት ለውሶ ነው የሚደመድም - ቴዎድሮስ::

አዎን የቴዎድሮስ ጥያቄና ሕልም የአዲሱ ትውልድ ፈተናና መፍትሄዎች ናቸው:: ቅዠት ላረረበት ትውልድ ደጉ ቴዎድሮስ ሕልም አለመለት:: ትናንት በዛሬ ተደገመ ማለት ይሆን? ሕልም ግን እንደፈቺው ነው አሉ ...ማን ያውቃል?

በጥያቄ ተጀምሮ በህልም የተደመደመው የደራሲው የግጥም መድበል ቅርፅና ይዘት ታድያ የድርሰቱን ሌሎች ሚስጥሮች ለመመርመር የሚያደፋፍር እንጂ " ብልቱን አገኘሁት " አሰኝቶ የንባብን አምሮት የሚያቅብ አይደለም::

ደራሲ ቴዎድሮስ በግጥም መድበሉ ውስጥ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ጥቂት ስንኞች በመቋጠር የትውልዱን ጥልቅ ፈተናዎች የዘረዘረና ያሳየበት ስልቱ እውነትም " ስነ ግጥም በጥቂት ቃላት ሰፊ ባህረ ሃሳብ ሊገለጥበት የሚችል ጥበብ ነው " ለሚለው የስነግጥም ባለሙያዎች አባባል በቂ ምስክርነት አለው::

ስነግጥም እንደሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች ሁሉ በቅርፅና በይዘት የሚገነባ ጥበብ ነው:: እንደደራሲው ችሎታና ብስለት የተለያዩ መልዕክትን የማስተላለፊያ ዘዴዎች መጠቀም የደራሲው ሙሉ መብትና ነፃነት ነው - ገደብ የለሽ:: በልዩ ልዩ ቅርፃዊ ዘዴዎች ያልታሸ ያገጠጠ ያፈጠጠ ደረቅ ይዘት ለተደራሲም እንጨት እንጨት ነው- የሚል:: አይዋጥም፣ አይስብም፣ አይማርክም፣ ይልቁንም ይተናነቃል፣ ይገፈትራል፣ ያስቀይማል:: ተደራሲን ከድርሰቱ ጫፍ እጫፍ ይዞ መጓዝ ይቅርና ደራሲውን ጭምር " ዓይንህ ላፈር " ብሎ መራገም ድረስ ሊገፉ ይችላል:: የደራሲን ምጥ ከእናት ምጥ ዓይነት ልዩ የሚያደርገውም ይህ ተደራሲን አስቀድሞ እያሰቡ የመጨነቅና የመጠበብ ሲቃ ነው::

በስነግጥም ቅርጽነት ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጉዳዮች ምት÷ ዜማ÷ ቁጥብነት እምቅነትና ለሰዋሰው ተገዢ አለመሆን ዋነኞቹ ናቸው:: " የእከሌ ግጥም ቤት አይመታም " ሲባል የስነግጥም ባሕርይ ከሚጠይቃቸው ዋነኛውን የስንኞችን የመጨረሻ ሆሄያት አለመስተካከል ለመጠቆም ነው:: አንድን ግጥም ለመገንባት በደራሲ የሚመረጡ ቃላት በስንኙ አደራደር ሂደት በዘፈቀደ የሚወረወሩ ሳይሆኑ ስነግጥም የሚጠይቃቸውን ቅርፆች እንዲያሟሉ ታስበባቸው በስልት የሚሰገሰጉ ናቸው::

ቤት መምታት የስነግጥም ዋነኛ ባሕርይ በመሆኑ ብዙውን ጊዜ ግጥሙ የሚፃፍበትን ቋንቋ ሰዋሰው አለመከተል በገጣሚ ስራ ውስጥ የተለመደ ተግባር ነው:: በቃላት አጠቃቀም ረገድ ሳይቀር አንዳንዴ ገጣምያን ፈንገጥ ብለው የሚታዩት ይህንኑ የቤት መምታት ዋነኛ ባህርይን ለማሟላት በሚያደርጉት ጥረት ምክንያት ነው:: አልፎ አልፎ ባንዳንድ ገጣሚያን ላይ " ቋንቋችንን አበላሹት " የሚል አቤቱታ መሰማቱ በዚሁ በቤት መምታት አስገዳጅነት የተነሳ በሚደረጉ ማፈንገጦች ስለሆነ ብዙም ልንደነቅ አይገባም:: ይህ ሲባል ግን ገጣሚ ሁሉ የደራሲ ነፃነቱን ምክንያት እያደረገ ከሚፅፍበት ቋንቋ ስርዓት ውጭ ያሻውን ማድረግ

የሚችል ነው ማለት አይደለም:: የሕዝብ ሃብት የሆነን ማናቸውንም ቋንቋ በፈለገው መንገድ የመምራት ነፃነት ያለው የጥበብ ሰው የለም:: ስነፅሁፉ ከሚቀርብለት ተደራሲ ቋንቋ እጅጉን ውጭ መሆንም በደራሲና በተደራሲ መካከል አለመግባባትን ጭምር ሊያስከትል  ስለሚችል ብቃት ያለው ደራሲ ሁሌም ከዚህ ዓይነቱ ተግባር የራቀ ነው የሚሆነው::

ሌላው የግጥም ዋነኛ ባሕርይ በቃላት አመራረጥ ረገድ ቁጥብና እምቅ መሆኑ ነው:: ገጣሚ እንደሌሎች የስነ ፅሁፍ ዘርፎች ይዘትን ለማስጨበጥ ሲል ቃላትን የመደጋገም ሰፊ ዕድል የለውም - በጥንቃቄ በተመረጡ ጥቂት ቃላት ነው መልዕክቱን ማስተላለፍ የሚችል:: ይህን ለማድረግም እምቅነት ያላቸው የውብና የምርጥ ቃላት መዝገበ ቃላት የመሆንን ያህል ይጠበቅበታል- የግጥም ደራሲ::

በሃገራችን በስነፅሁፍ ተግባር ተሰማርተው አንቱ የተሰኙ ድርሰቶችን በተደጋጋሚ ያቀረቡልንን ደራሲያን በአብዛኛው የምናውቃቸው በቃላት አመራረጣቸው ጭምር ነው:: ብዙዎቹ የግድ በስራዎቻቸው የመጀመሪያ ገጽ ላይ የድርሰቶቻቸው ባለቤት መሆናቸውን መፃፍ አያሻቸውም ነበር:: አፈሩን ያቅልልለትና ብላቴን ጌታ ፀጋዬ ገብረመድህን ዋቀዮ በግጥሞቹ ውስጥ በሚጠቀማቸው ምርጥ ቃላት ኃያልነት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተለይቶ ከታወቀ ከአራት አሰርታት ዓመታት በላይ ተቆጥረዋል:: የቀሩትም እነከበደ ሚካኤል መንግስቱ ለማ  ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው አቤ ጉበኛ ደበበ ሰይፉ ፈቃደ አዘዘና ሌሎችም በዚህ መስክ ተጠቃሾች ናቸው - ሁሉም የራሳቸው ስልቶች ነበሯቸው/አሏቸው::

ቴዎድሮስ አበበ በበኩር ስራው በ " ፈተና " ውስጥ በአብዛኛው የዕለት ተዕለት የሰርክ ቃላትን በመጠቀም ነው - ቁምነገሮቹን ሲያካፍለን የምናየው:: ይህም ተደራሲውን እስከመጨረሻዎቹ የድርሰቱ ገፆች ይዞ ለመጓዝ ሲል የመረጠው ተገቢ ዘዴ ነው:: ከዚህም በላይ የቴዎድሮስ ግጥሞች ቤት በመምታት ዜማ በመጠበቅና ድግግሞሽን በማስወገድ ረገድ አንድ ጥሩ ገጣሚ ሊከተላቸው የሚገቡ የስነ ግጥም ሕጎችን አሟልተው የሚገኙ ናቸው::

የቴዎድሮስን የግጥም መድበል ልዩ ከሚያደርጉት አዲስ ቅርፆች አንዱ ደራሲው ለዛሬው እሱነቱ ባለውለታዎቹ በግጥም መድበሉ እያለፈ እያለፈ የሰደራቸው ውዳሴ- መምህር ግጥሞቹና መታሰቢያ ስንኞቹ ናቸው:: በግጥሞቹ ለአያሌዎች መታሰቢያ የፃፋቸው ግጥሞቹ ቴዎድሮስ ውለታ እንደሚከብደውና በሰብዕናው ላይ በቀጥተኛም ሆነ በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ ያሳደሩበትን የማይረሳ መሆኑን ሲያስገነዝብ ለአንባቢ ደግሞ ቀደምቶቻችንን መርሳት የሌለብን ከነሱም የምንማረው ቁም ነገር መኖሩን እንዲሁም መነሻችን እኒሁ የጥንት የጥዋቶቹ መሆን እንዳለባቸው በእጅ አዙር የነገረበት መንገድ ነው:: ሌላው ቀርቶ የነገ የሃገር ተስፋዎቹን የእህቱን ልጆች የእምነትን ልዩንና ሕያዊትን እንኳ ከቶም አልዘነጋቸውም - ቴዎድሮስ:: እንዳውም " ...የሚፈነጥቁት ብሩኅ ተስፋ ከፊቴ ለተዘረጋው የጨለመ መንገድ መብራት እየሆነኝ በታላቅ ደስታና በጠነከረ መንፈስ አብሬአቸው እጓዛለሁ " ሲል የፈተናችን አሸናፊዎች እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠቁመናል::

ቴዎድሮስ ሌላ የዋለልን ውለታ ቢኖር ቀደምት ከሚላቸው ከአንዳንዶቹ ታላላቅ ኢትዮጵያውያን ጋር በፎቶግራፍ ጭምር ሊያስተዋውቀን በብርቱ መጣሩ ነው:: በዚህም ሳይታቀብ የባለታሪኮቹን ታሪካዊ ድርጊታቸውን እየጠቀሰ፣ የጥልቅ አስተሳሰብ አምራቾቹን ደግሞ ካፈለቋቸው ጥልቅ ሃሳቦች በጥቂቱ እየቆነጠረ በመድበሉ ውስጥ በተገቢው ቦታ በማስቀመጥ የደራሲን ቀዳሚ የማዝናናት፣ ለጥቆም የማስተማር ተግባር በሚገባ ተወጥቷል - በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ይሏል ይህ ነው:: ቀላል ግን አሳቢ አዕምሮ የሚሻ ድንቅ ጥበብ::

በይዘት አንፃር የተመለከትነው እንደሆን እንደብዙዎች በባዕድ ሃገር እንደሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ፀሐፊዎች የቴዎድሮስም ግጥሞች በተቃውሞ ሥነፅሁፍ ስር ሊመደቡ

የሚችሉ ናቸው። አብላጫዎቹ ግጥሞቹ የሃገሩን ሕዝብ ብሶት ስቃይና መከራ የሚዳስሱና የሕዝብ አስተዳዳሪዎች ነን የሚሉትን የሚሞግቱ ስራዎች ናቸው። ለአብነት ገፅ መቶ ሃያ ሁለት ላይ የሰፈረው " ተጠየቅ " በሚል ርዕስ የቀረበው እንጎቻ ግጥሙ፥

ልምራህ የምትለውን ሕዝብ
ከልብህ ካልወደድከው፤
ልፈውስ ያልከውን ወገን
ታዛዥ አገልጋይ ካልሆንከው፤
ላንጽህ ያልከውን ትውልድ
በሥልጣንህ ካመከንከው፤
የለውጥ አርበኝነትህ
መሪነትህ ምኑ ላይ ነው?

እያለ ሃገር በቀል በሆነው የቃላዊ ስነጽሁፍ ቅርፅ " በላ ልበልሃ " ስልት የሃገሩን መሪ ተብዬዎች ደፍሮ ይጋፈጣቸዋል። ይህ ግጥም በጥቂት ምርጥ ቃላት ሰፊና ጥልቅ ሃሳቡን ማስተላለፍ የቻለበት የእሱነቱ መገለጫም ሆኗል።

ሌላው የተቃውሞ ስነጽሁፍ አካል ድርሰቱ ምሳሌ በቅርቡ የሕዝቧ ድምጽ ባደባባይ ሲሰረቅና አሻፈረኝ ባይ ቆራጥ ልጆቿ በጥይት ሲጨፈጨፉ ስታይ በምሬት የተንሰቀሰቀችው ሃገሩን ኢትዮጵያን የገለጸበት ግጥሙ ነው።

ለምን አታለቅስ?
ለምን አታነባ?
ተስፋዋ ሲቀጠፍባት
ወደመቃብር ሲገባ
ለምን አታነባ?
ኢትዮጵያ?
ለምንስ ቅስሟ አይሰበር?
በመሪር ሃዘን ተሸንፋ
የዐይኗ ተስፋ የሆነው
ወጣት ትውልዷ ሲጠፋ?
ለምን አትከፋ?
እንዴትስ ጭንቀት አይውጣት
ዕንባዋንስ ምን ሊገደው?
የአምባገነን የግፍ ጥይት
ተስፋዋን ሲደበድበው?
ለምን አታለቅስ?
ለምንስ አትከፋ?
የገነጠላት ባንዳ
ዳግም ተስፋዋን ሲያጠፋ?
ምነው አይከፋት?
ሐዘኗ አይከብድባት ( ገጽ 136 )

እያለ የእናቱን እንባ በብዕሩ ሊያብስ ሞክሯል - ቴዎድሮስ። የሃገሩን ጠላቶችም ሳይፈራና ሳይደብቅ፥

እኛን እያበላ ኬክና ባቅላባ
ንግዱን አጧጡፎ መሃል አዲሳባ
ለካስ አቶ እንቶኔ ያካብት የነበር

የደም ገንዘብ ኖሯል መሸጫ የድንበር። ( ገጽ 33 )

እያለ እያዋዛ ምስጢሩን ነግሮናል - ሰሚ ከተገኘ። የዕብድ ገላጋይ መሪ ተብዬውን ሳይቀር፥

የዘረኝነት ፈላስፋው
    የመከፋፈል ሊቁ
አንድነትን ለመስበክ
    ወደ ሩቅ ምስራቅ መዝለቁ...
ምን ይባላል? ( ገጽ 114 )

ዕብደት - ሲል ተሳልቆበታል - በድርሰቱ።

" የዕንባ ጉዞዎች " በተሰኘው ግጥሙም ባንድ ወቅት የረሃብተኛ ወገኖቹን ስቃይ እያየ ቢያነባም ሊደርስላቸው ባለመቻሉ የልቡን መድማትና የአዕምሮውን መቁሰል ይነግረናል - በጸጸት እንዲህ እያለ ...

... እኒያ ምስኪኖች
የኩታበር ነዋሪዎች
ባዶ ከረጢት ተሸክመው
በረጅም ጉዞ ተዳክመው
ሲያመሩ ያገኘኋቸው
ወደየጎጇቸው ...
የእርዳታ እህል ዜና ሰምተው
ከጎረቤት ተጠራርተው ...
ዶንያቸውን
ከረጢታቸውን
በተስፋ ሞልተው ነበር
    ከቤታቸው የወጡ
የእርዳታ እህል ሊያመጡ።
ግን ... ሳይሳካላቸው ቀርቶ
ጧት ይዘውት የወጡት ተስፋ
    እንደከረጢታቸው ተራቁቶ
ሲመለሱ ነበር ያየኋቸው
ወደ ተራበች መንደራቸው።
ሌሎቹም ትዝ ይሉኛል
    በዐይነ ሕሊናዬ የሚታዩኝ
በዕንባ ጉዞዎች ያጋጠሙኝ
ግን... ምን ዋጋ አለው?
የሃገር የወገን ፍቅር
    ዕንባ ቢሆን መለኪያው
ጸጸት ቢሆን ኖሮ መለያው
ዕረፍት ባገኘ ነበር ሕሊናዬ
ዕንባ ባጀበው ጉዞዬ። ( ገጽ 66 )

የዚህ ግጥሙ ስልት ለየት ባለ የስንኝ አቆጣጠር ዘይቤ በሰፊው በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚታወቁትን የ " አፈር ያነሳ ስጋ " እና " የተጓጓጠ ልብ " ደራሲውን የቀለም አባቴን የሰይፉ መታፈሪያ ፍሬውን ኮቴ የሚከተል ሁኖ በማግኘቴ ደስ ብሰኝም ከምስጋናው ረድኤት ስለነፈጋቸውና ከቀደምቶቹ ዝርዝር ውስጥ ስላላካተታቸው ግን በመጠኑም ቢሆን

ማዘኔን አልሸሸገውም - ለቴዎድሮስ። ጻሩ ሁሉን አመስግኖ እንዴት ይቻላል? ይል የለ ያገራችን ሰው።

ነገር ግን ባለቅኔው ሰይፉ እንደፀጋዬ ቤት ሁሉ " የሰይፉ ቤት " ሊሰኝ የሚበቃ ልዩ የስንኝ አደራደር በመጠቀምና ይህንኑም ስልት ለአማርኛ ስነግጥም በማበርከት ረገድ ለአያሌ ወጣት ኢትዮጵያውያን ገጣምያን በአርአያነት የሚጠቀሱ እውቅ ደራሲና የጥሩ መምሕር ምሳሌ ናቸው - ብዙ አርሰው ሊያመርቱ ከሚችሉበት የስነጽሁፍ እርሻ ከሌሎች አርባ አንድ መምህራን ጋር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባይባረሩ ኖሮ። ይሁንና ሰይፉን በቴዎድሮስ ስራዎች ውስጥ አሻግሬ በማየቴና ዛሬም በርትተው እየጻፉና እያስተማሩ መሆኑን ሳውቅ ሁሌም እፅናናለሁ። እሰየው ሰይፉ… እሰየው ቴዎድሮስ።

ታድያ ቴዎድሮስ ከቀደምት ጸሓፍት የአፃፃፍ ስልትን ብቻ ሳይሆን ፈሪሃ እግዚአብሐር ባሕሪያቸውንም መውረሱ በስራዎቹ ፍንትው ብሎ የሚታይ እጡብ ድንቅ ባሕርይው ነው። እንደቀደምቶቹ ደራሲዎቻችን ሁሉ ቴዎድሮስም " አስጀምሮ ላስፈፀመኝ እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን " ብሎ አማትቦ ነው - ወደ ጉዳዩ የሚንደረደር። ከዚህም በላይ በቀጥተኛ መንገድ ርዕስ ሰጥቶ ስንኝ የቋጠረባቸው " ዕንቁ " " ምስጋና " " ዋልድባ " " " አዳኞቹ " እና " ሊቅ " በተሰኙ ርዕሶች የቀረቡት ግጥሞቹ ለፈጣሪው ለሃይማኖቱ ለደጀ ሰላምና ለአገልጋዮቿ ያለውን ከበሬታ የገለፀበት ስራዎቹ ናቸው። በተለይ " እናስበው " በሚል ርዕስ በፃፈው ግጥሙ ምናልባትም … ይለናል - የአዲሱን ትውልድ ህሊና በመማፀን ስሜት …

> የትግላችን ፍሬ የዘገየው
> ድካማችን የመከነው
> ተስፋችን የዳመነው
> ሸክማችን የከበደው
> እምነታችን የከሳው ÷ አንድነታችን የቀጨጨው
> ችላ ስላልነው ይሆናል … ከመሀላችን ስላራቅነው።
> ኢትዮጵያ የአምላኳ ናት የፈጣሪነቱ መመስገኛ
> የፈሪሀ እግዚአብሔር ምንጭ የግማደ መስቀሉ መገኛ።
> ስለሆነም … እናስበው
> ምንጫችንን አናድርቀው። ( ገጽ 124 )

እያለ ፊታችንን ወደ ፈጣሪ እንድንመልስ ጋብዞናል- ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ … ። ከእንግዲህ የራሳችን ጉዳይ ነው።

በአጠቃላይ የቴዎድሮስ የግጥም መድበል " ፈተና " የድርሰቱ ባለቤት የሃገሩን ምጥ አብሮ ያማጠበት፣ የወገኑን ብሶት መከራና ስቃይ በድፍረት ያስተጋባበት፣ ጉድፉን ሳይቀር እየነቀሰ በማሳየት የበኩሉን መፍትሔ ያካፈለበት፣ አበክሮም ለዘመኑ አዲስ ትውልድ የኅሊና ደወል ያሰማበት የበኩር ስራው ነው - ይበል የሚሰኝ። ደራሲውን እደግ ተመንደግ እያልሁ እንደድርሰቱ መደምደሚያ እኔም " አቡነ ዘበሰማያት … ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት " እላለሁ።

ብሌን ዓለማየሁ
ጁላይ 2006